spl.org

# አንድ ላይ በቤት ውስጥ መማር


## ለሙዓለ ሕፃናት ተማሪዎች እና ለቤተሰቦቻቸው የቅድመ ንባብ እና ጽሑፍ መልመጃዎች

ስለ እናንተ እናስባለን ፥
ናፍቃችሁናል።
በቅርቡ ደግመን
እንደምናያችሁ ተስፋ
እናደርጋለን!

# ከውስጥ የሚገኘው

አንባቢን ለማሳደግ የሚጠቅሙ 5 መልመጃዎች


- ማውራት
- መዘመር
- ማንበብ
- መጫወት
- መጻፍ



ጉርሻ፡- ሳይንስ

የፊደል ካርዶች

የእንስሳ ካርዶች





# አንባቢ ለማሳደግ የሚጠቅሙ 5 መልመጃዎች

1. ማውራት:-

   ማውራት ቋንቋን እና የቃላትን ችሎታን ያዳብራል

2. መዘመር:-

   መዘመር ልጆች የተለያዩ ድምፆችን እንዲሰሙ ያደርጋል

3. ማንበብ:-

   በመጽሐፎች ውስጥ ያሉትን ሥዕሎች በመጠቀም ታሪኮችን ማንበብ ወይም መንገር ይለማመዱ

4. መጫወት:-

   መጫወት የልጅዎ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ አካል መሆን አለበት

5. መጻፍ:-

   በመሳል እና ሥዕል በመጫጫር ጡንቻዎችን ይገንቡ

# ቤት ውስጥ አብረው ያውሩ

ማውራት፣ ነገሮችን መሰየም እና የተለያዩ ቋንቋዎችን በቤትዎ ውስጥ መጠቀም ልጅዎን የቃላት ችሎታውን እንዲገነባ ይረዱታል። ልጅ ብዙ ቃላት በሰማ ቁጥር፣ የቃላት ችሎታው እየጨመረ ይሄዳል፣ ማንበብ በሚጀምርበት ጊዜም ቃላትን በሆሄ ድምፅ እያወጣ ለማንበብ ይቀለዋል።

## አብረን እንንቀሳቀስ፡-

አንዳንዴ ወደላይ፣ ወደላይ፣ ወደላይ እንጠራራለሁ
(እጆቼን እና ክንዴን ወደላይ ከፍ አደርጋለሁ)


አንዳንዴ እንደ ትንሽ ትንሽ ትንሽ ጥቅልል እላለሁ
(ጎንበስ ብዬ እንደ ኳስ ሰውነቴን ክብ አደርገዋለሁ)

አንዳንዴ ወደጎን እዘረጋለሁ - ክንዶቼን ክፍት አድርጌ
(መቆም እና ክንዶችን በሰፊው መክፈት)

አንዳንዴ ከጎን ወደጎን እወዛወዛለሁ
(ክንድ እና ሰውነትን ከጎን ወደጎን ማወዛወዝ)

አንዳንዴ እዘልና ሰማይን እነካለሁ
(እጅን ወደላይ ከፍ አድርጎ መዝለል)

ከዚያ ወደመሬት ተንሳፍፌ እወርድና ኡፍ ብዬ እተነፍሳለሁ
(ጣቶችን እስከ እግር ድረስ አወዛውዞ መቀመጥ)



## አብሮ ማውራት፦

ከልጅዎ ጋር አብረው በእግር ዘወር ዘወር ይበሉ (ከቤት ውስጥም ውጭም ሊሆን ይችላል)። ስለሚያዩት፣ ስለሚዳስሱት፣ ሰለሚቀምሱት እና ስለሚሰሙት ነገር ያውሩ። የተለያዩ ቅርጾችን እና ቀለማትን በመጠቆም ያሳዩ። ነገሮችን የመቁጠር ጨዋታ ይጫወቱ።

ምግብ በሚያዘጋጁበት ጊዜ፣ እያንዳንዱን የምግብ አሠራር ሂደት ያብራሩ። የተለያዩ ንጥረ ነገሮች ምን እንደሚመስሉ፣ ሲነኩ ምን እንደሚሰማ፣ ሽታቸው እንዴት እንደሆነ ያብራሩ። ስለሚሠሩት ምግብ ያላችሁን ስሜት ወይም ትውስታ ያካፍሉ።

መተኛ ሰዓት ሲደርስ፣ ታሪክ ፈጥረው ወይም ከልጅዎ ጋር ምን ሲያደርጉ እንደዋሉ ያውሩ።



## የመልመጃ ካርታ መዝናኛ፦

ከእንስሳት ካርዶች አንድ እንስሳ ይምረጡ፣ ግን ለልጅዎ አያሳዩት። እንስሳው ምን እንደሚመስል ለልጅዎ ያስረዱት እና ልጅዎ የሚያስረዱትን እንዲሥል ያድርጉት። ስለዚያ እንስሳ ከልጅዎ ጋር አብረው ታሪክ ይፍጠሩ።

# ቤት ውስጥ አብሮ መዘመር

መዘመር ቋንቋን ቀስ ተብሎ እንዲነገር ስለሚያደርግ ልጆች በቃላት ውስጥ ያሉ ትንንሽ ድምፆችን መስማት ይችላሉ። ይሄ በተለያዩ ድምፆች እንዲጫወቱና አዳዲስ ቃላት እንዲማሩ ይረዳቸዋል።

## አብረን እንንቀሳቀስ፦


( ይህንን ከታዳጊ ልጅ ጋር ወይም ከሙዓለ ሕፃናት ተማሪ ጋር ከሆነ የሚያደርጉት አብራችኋቸው ይቁሙ። ከሕፃን ልጅ ጋርም አብረው ሊያደርጉ ይችላሉ፣ ፊታቸውን ወደ እርስዎ አዙረው ታፋዎ ላይ አስቀምጠዋቸው ወይም ደግሞ ሰውነታቸውን እርስዎ ላይ እያንቀሳቀሱ እንዲህ ማድረግ ይችላሉ)


ራስ፣ ትከሻ፣ ጉልበት እና የእግር ጣት፣ ጉልበት እና የእግር ጣት

ራስ፣ ትከሻ፣ ጉልበት እና የእግር ጣት፣ ጉልበት እና የእግር ጣት

ዐይን እና ጆሮ እና አፍ እና አፍንጫ

ራስ፣ ትከሻ፣ ጉልበት እና የእግር ጣት፣ ጉልበት እና የእግር ጣት!






spl.org

## አብረው መዘመር፡-

እንደ ዳይፐር መቀየር እና ምግብ ማብላት ወይም አንድ ሥራ ወደ ሌላ ሥራ በሚቀይሩበት ጊዜ ያሉ የቀን ተቀን ሥራዎች እየሠሩ ለልጅዎ ይዘምሩ። ከሙዚቃው ምት ጋር በሚችሉበት ጊዜ አብረው አስዘልሏቸው።

የሚወዱትን ሙዚቃ በየተራ እየቀያየሩ ያሰሟቸው።

እንደ ቤተሰብ ሙዚቃ መፍጠር ይችላሉ? እንደፈለጉ አዝናኝ ማድረግ ይችላሉ ቃላትም መጠቀም አያስፈልግዎትም!



## የመልመጃ ካርታ መዝናኛ፡-

የፊደል ካርዶችን በመጠቀም ኤቢሲ መዝሙርን ዘምሩ፣ እያንዳንዱን ፊደል ሲዘምሩ ፊደሉ ላይ ይጠቁሙ።

# ቤት ውስጥ አብሮ ማንበብ

በየቀኑ ቤት ውስጥ አብሮ ማንበብ ልጆችን ለማንበብ እንዲዘጋጁ የሚያደርግ እጅግ ጠቃሚ ልማድ ነው። ከ ማንበቢያ መጻሕፍት በተጨማሪ፣ በቀን ውስጥ የሚሠሩት ሥራ ውስጥ ያሉ ቃላትን እየጠቀሙ ያንብቡ። ልጆች በዙሪያቸው ያሉትን ኅትመቶች እንዲያስተውሉዋቸው ይረዳል።

## አብረን እንንቀሳቀስ፦

ወደ ቤተመጻሕፍት እየሄድን ነው
(በቆሙበት መራመድ)

መጻሕፍት መምረጥ
(በሁለቱም እጅዎ መጽሐፍ እየመረጡ እንዳሉ ማስመሰል)

እናስመዘግባቸዋለን
(ሁለቱንም እጅ ወደፊት መጠቆም)

አስመዝግበትን ይዘን እንሄዳለን!
(በሁለቱም አውራጣትዎ ከትከሻዎ በላይ አድርገው ወደኋላ መጠቆም)

መዝገበ ቃላቱን ሰላም ልንል እንሄዳለን
(ለሰላምታ እጅዎን ያወዛውዙ)

መጻሕፍት መምረጥ
እናስመዘግባቸዋለን
አስመዝግበትን ይዘን እንሄዳለን!

## አብሮ ማንበብ፡-

ከልጅዎ ጋር አብሮ በመሆን የጋዜጣ ወይም የመጽሔት ዓምድ ያንብቡ፣ ከልጅዎ ስም የመጀመሪያ ፊደል ጋር በተመሳሳይ ፊደል የሚጀምሩ ቃላቶችን በሙሉ እየመረጡ ያክብቡባቸው።

የትኛውንም እና ማንኛውንም ነገር ያንብቡ።

- እራት ለመሥራት የምግብ አዘገጃጀት መመሪያ የሚጠቀሙ ከሆነ፣ እያንዳንዱን ሂደት ለልጅዎ እያነበቡ ይሥሩ።
- ምግብ ለማብሰል ንጥረ ነገሮችን በሚሰበስቡበት ጊዜ መሰየሚያዎቹን ለልጅዎ ጮክ ብለው ያንብቡ። እነርሱም የሚያስታውሷቸውን ፊደላት መጠቆም ይችላሉ!
- የመንገድ ምልክቶች ላይ ያሉትን ቃላት በመጠቆም ያሳዩ።

መጻሕፍት በሚያነቡበት ጊዜ፣ ልጆችዎ እርስዎ የሚያነቡት ሥዕሎቹን ሳይሆን ፊደላቱን እያነበቡ እንደሆነ እንዲያዩ የሚያነቡት ቃላት ለይ ጣትዎን ያስደግፉ። ይህ ቋንቋው የሚነበብበትን አቅጣጫ እንዲረዱ ያግዛቸዋል (ለምሳሌ እንግሊዘኛ ከግራ ወደቀኝ ነው የሚነበበው)።

## የመልመጃ ካርታ መዝናኛ፡-

የፊደላትን ቅርጽ በቤት ወስጥ ወይም ውጭ ይፈልጉ የፊደል ካርዶችን በመያዝ በቤት ውስጥ ወይም በሰፈር ውስጥ ከፊደላቱ ጋር ተመሳሳይ ቅርጽ ያላቸውን እቃዎች ይፈልጉ። ሲያገኟቸው ይሰይሟቸው። ለምሳሌ፣ “Y” ፊደልን የሚመስል እንጨት፣ “O” ቅርጽ የሚሠራ የእጅ አምባር፣ ወይም “S” ቅርጽ ሊሠራ የሚችል የጫማ ማሰሪያ ክር መፈለግ።



# ቤት ውስጥ አብረው ይጫወቱ

ጨዋታ ለልጆች እራሳቸውን እንዲገልጹ እና ሐሳባቸውን ወደ ድርጊት እና ወደ ቃላት እንዲቀይሩ ይረዳቸዋል። ጨዋታ ልጆች የሚነበቡ እና የሚነገሩ ቃላት እውነተኛ እቃዎችን እና ልምዶችን እንዴት እንደሚገልጹ እንዲረዱ ያግዛቸዋል።

## አብረን እንንቀሳቀስ፡-

እጅ ወደላይ፣ ነቅነቅ ነቅነቅ ነቅነቅ
(እጅ ወደላይ አድርጎ መነቅነቅ)

እጅ ወደታች ነቅነቅ ነቅነቅ ነቅነቅ
(እጅ ወደ ጉልበት ዝቅ አድርጎ መነቅነቅ)

መሽከርከር ነቅነቅ ነቅነቅ ነቅነቅ
(ሰውነትን እያሽከረከሩ እጅን መነቅነቅ)

መሬት መንካት ነቅነቅ ነቅነቅ ነቅነቅ
(መሬት መንካት፣ እጅ መነቅነቅ)

## አብሮ መጫወት:-

ይሄንን ጨዋታ  አየሁ  ቀለም በመጠቀም መጫወት። "በትንሿ ዐይኔ ቢጫ የሆነ ነገር አየሁ" ማለት። ቢጫ የሆነ እኔ ያይሁት ነገር የቱ ጋር የታያል?"

ይሄንን ጨዋታ  አየሁ  ፊደላት በመጠቀም መጫወት። ለምሳሌ "በትንሿ ዐይኔ በ ቢ ፊደል የሚጀምር የሆነ ነገር አየሁ" ማለት። በ ቢ ፊደል የሚጀምር እኔ ያይሁት የሆነ ነገር የቱ ጋር የታያል?"


ድንገት ቀጥ የሚለወንዳንስ መጫወት። የሚወዱትን ሙዚቃ ከፍተው ይደንሱ። ልክ ሙዚቃው ሲቆም፣ ሁሉም ደናሾች መንቀሳቀስ ያቆሙ እና ሙዚቃው እንደገና እስኪጀምር ባሉበት ቀጥ ይላሉ።

ከጓደኞቻቸሁ ጋር ስትጫወቱ የሚያሳይ ሥዕል ሣሉ። የትኞቹ ጓደኞቻቸሁ ናፍቀዋችኋል? ከእንደገና ስትገናኙ ምንድነው ማድረግ የምትፈልጉት? አንድ ጓደኛችሁ ጋር ስልክ በመደወል ንገሯቸው።

## የመልመጃ ካርታ መዝናኛ:-

ልጅዎ ከእንስሳ ካርዶች አንድ እንስሳ እንዲመርጥ ያድርጉ። ስለዚያ እንስሳ ታሪክ እየተረኩ ልጅዎ ያንን እንስሳ እንደሆነ አድርጎ እንዲያስመስል ይጠይቁት። እንደ እንስሳው መንቀሳቀስ፣ እንድ እንስሳው ዓይነት ድምፅ ማውጣት፣ እና ታሪኩን በድርጊት ማሳየት።

የፊደል ካርዶቹን በመጠቀም የተለያዩ ፊደላትን በክፍሉ አካባቢ ያስቀምጡ። ከዛ ፊደሉን ይጥሩ እና ልጅዎ ወደ ጠሩት ፊደል እንዲዘል ያበረታቱት።



# በቤት ውስጥ አብሮ መጻፍ።

እርሳስ ከመያዝ እና ከመጫጫር፣ ወደ ፊደላት እና ቃላት መጻፍ፣ ልጆች ከሁለት ዓመታቸው ጀምሮ የጽሑፍ ችሎታቸውን መለማመድ ይጀምራሉ። መሞነጫጨር ልጅዎ ማንበብ እና መጻፍ እንዲችል ይረዳዋል!

## አብረን እንንቀሳቀስ፦

እንደ ዛፍ ረጅም፣ ምን ያህል መርዘም ይቻላል?
(ቀጥ ብሎ በመቆም እጅን ወደ ጣራ መዘርጋት)

እንደ ቤት ሰፊ፣ ምን ያህል ሰፊ መሆን ይቻላል?
(እጅ እና እግርን ከፍቶ ወደጎን ሰፋ አድርጎ መወጠር)

እንደ መርፌ ቀጭን፣ ምን ያህል ቀጭን መሆን ይቻላል?
(ቀጥ ብሎ በመቆም የእጅ ጣትን ወደ ወለል መጠቆም)

እንደ አይጥ ትንሽ፣ ምን ያህል ትንሽ መሆን ይቻላል?
(እንደ ትንሽ ኳስ ክብ መሥራት)

እንደ ዛፍ ረጅም፤ እንደ ቤት ሰፊ፣ እንደ መርፌ ቀጭን፣ እንድ አይጥ ትንሽ
(እያንዳንዱን መንጠራራት እንደፈለጉ እየደጋገሙ መሥራት ይቻላል!)


spl.org

## አብሮ መጻፍ፡-

ልጅዎ መጫጫር እንዲማር በቤትዎ ውስጥ እርሳስ ከለር እና ወረቀት ይኑርዎት። እርሳስ ከለር መያዝ እና መጫጫር ልጅዎ አንድ ቀን እንዲጽፍ የሚረዱትን የሞተር ክኅሎቶችን ለማዳበር የመጀመሪያ እርምጃዎች ናቸው!

ልጅዎ ቅርጾችን እንዲለይ ይርዱት። አንድ ላይ ቅርጾችን መሳል ወይም መጽሐፍ ላይ መጠቆም ይለማመዱ። ልጆች ፊደላትን በመጀመሪያ እንደ ቅርጽ ነው የሚያዩአቸው።

ልጅዎ ስሙን መጻፍ እንዲለማመድ ያድርጉት።  ስማቸው የመጣበትን ታሪክ ይንገሯቸው። ከስማቸው ጋር በአንድ ዓይነት ፊደል የሚጀምሩ ቃላትን ይጠቁሙላቸው።



## የመልመጃ ካርታ መዝናኛ፡-

ልጅዎ ከፊደል ካርዶች ላይ የስሙን ፊደል እንዲመርጥ ይርዱት። ከመጀመሪያ ስማቸው ጋር በተመሳሳይ ፊደል የሚጀምሩ ስም ያላቸው እንስሳትን ያስቡ እና ስለዚያ እንስሳ ታሪክ እንዲፈጥሩ ይርዷቸው። ታሪኩን በራሳቸው እርሳስ ከለር እና ወረቀት ላይ እንዲጽፉ ወይ እንዲጫጭሩ እንዲሁም ሥዕል እንዲሥሉ ይርዷቸው። ሲጨርሱ ታሪኩን መልሰው ያንብቡላቸው። ወይም ታሪኩን ለእርስዎ እንዲያነቡ ያድርጓቸው!

# በቤት ውስጥ ሳይንስን በአንድነት


ጥያቄዎችን መጠየቅ እና ስለ ዓለም ያላቸውን ምልከታ መግለጽ ልጅዎ በዙሪያው ስላለው ነገር ሁሉ ትርጉም የሚሰጥበት መንገድ ነው። አብራችሁ የምታዩትን እና የሚያጋጥማችሁን ነገር ለማስረዳት ጊዜ ይውሰዱ ፣ እና ንፅፅር ያድርጉ ወይም ልዩነቶችን ይጠቁሙ። ትናንሽ ልጆች ስለሁሉም ነገር የማወቅ ጉጉት አላቸው፤ እነሱ ተፈጥሯዊ ሳይንቲስቶች ናቸው!

## አብረን እንንቀሳቀስ፡-

[ቆሞ ከግጥሙ ጋር አብሮ መደነስ]

ዙም፣ ዙም፣ ዙም ወደ ጨረቃ ልንሄድ ነው።
ዙም፣ ዙም፣ ዙም በቅርቡ ልንሄድ ነው።
ጉዞ ለመሄድ ከፈለጉወደ ሮኬት መርከቤ ግቡ።
ዙም፣ ዙም፣ ዙም ወደ ጨረቃ ልንሄድ ነው።
5, 4, 3, 2, 1... ወደጉዞ!

[በጣቶችዎ ቀስ ብለው ቆጥረው ይዝለሉ!]



spl.org

# ሳይንስ በአብሮነት

ወደ ውስጥ (ወይም በውጭ) ፍለጋ ይሂዱ እና ተመሳሳይ ነገሮችን ይፈልጉ፡- ጥቃቅን ነገሮች ፣ አረንጓዴ ነገሮች ፣ ለስላሳ ነገሮች ፣ እና ሌላ ሊያስቡት የሚችሉትን ነገር ሁሉ!

አብራችሁ በምትመገቡባቸው ምግቦች ላይ የመቅመስ ሙከራ ያዘጋጁ። ዓይኖችዎን ጨፍነው በእያንዳንዱ ጉርሻ የሚያጋጥማችሁን ጣዕሞች ፣ ሽታዎች እና የመሻከር ወይም የመለስለስ ጣዕም ይግለጹ።

በሕይወትዎ ውስጥ ያጋጠመዎትን የሆነ ችግር እንዴት እንደፈቱ ታሪክዎን ያካፍሉ። ወይም፣ እንድ በጣም ያጓጓዎ ከዛም በደንብ የተማሩትን ነገር ይግለጹ።

በቤት ውስጥም ሆነ በውጭ የሚያዩትን አንድ ነገር በሥዕል ይሣሉ። ልጅዎ ከሕይወት ላይ እንድን ነገር ለመሳል ሲሞክሩ ያሰፈሩት ዝርዝሮች ላይ ይነጋገሩ።

## የመልመጃ ካርታ መዝናኛ፡-

የእንስሳት ካርዶቹን በመጠቀም ከልጅዎ ጋር አብረው ወደ ተለያዩ ምድቦች ይመድቧቸው። ቢጫ የሆኑ እንስሳት የትኞቹ ናቸው? አራት እግር ያላቸው እንስሳት የትኞቹ ናቸው? የሚፈልጉትን ማንኛውንም ምድብ ይፍጠሩ!



Proudly sponsored by

The Seattle Public Library Foundation

www.SupportSPL.org